## ማውጫ


መግቢያ ..... 2
ክፍል አንድ ..... 3
አጠቃላይ ሁኔታ ..... 3
1.1 ዓላማ ..... 3
1.2 የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማ፤ ..... 3
1.3 ከሥልጠናው የሚጠበቅ ውጤት ..... 3
1.4 የሥልጠናው ወሰን ..... 3
1.5 የሥልጠናው ተሳታፊዎች ..... 4
1.6 ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ ..... 4
1.7 ትርጉም ..... 4
ክፍል ሁለት ..... 5
ተርን ኦቨር ታክስ ..... 5
2.1 የተርን ኦቨር ታክስ ምንነት ..... 5
2.2 የታክሱ መጣኔ ..... 5
2.3 የታክሱ ስሌት መሠረት; ..... 5
2.4. ከታስ ነፃ ስለመሆን ..... 5
ክፍል ሶስት ..... 7
3.1 ታክሱን ማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት ..... 7
3.1.1 የሂሳብ ጊዜ ማለት ..... 7
3.1.2 የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን ..... 7
ማጠቃለያ ..... 8
ማጣቀሻ ..... 8

**መግቢያ**

የታክስ ጉዳዮች ትምህርት እና መረጃ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት የተቋሙን በተገልጋይ ግንኙነት አመራር ልቀት የትኩረት መስክ የተቀረጹ እቅዶችን ለማስፈጸም የተለያዩ ሥራዎችን አቅዶ እየሠራ ይገኛል፡፡ የዳይሬክቶሬቱ የትኩረት አቅጣጫ ታክስ ከፋዮች ከታክስ አስተዳደሩ ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲሁም አጠቃላይ ማሕበረሰቡ በተርን ኦቨር ታክስ ዙርያ ያለው ግንዛቤ እንዲጨምር እና የሚጠበቅበት ግበር በወቅቱ እንዲከፍል ነው፤

በዚህም መሠረት በ 2008 በጀት ዓመት ተሻሽሎ የወጣው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 611/2008 እና አዋጅ ቁጥር 308/2002 ዙሪያ በተዘረጉ የአሠራር ሥርዓቶች ላይ አገልግሎት ሰጪውም ሆነ ተቀባዩ የጋራ ዕውቀትና መግባባት እንዲኖራቸው በተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን ዘርግቶ ለተገልጋዩ ተደራሽ ለማድረግ ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ጋር ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡በመሆኑም እነዚህን መሠረት በማድረግ ለግብር ከፋዮች ለማሠልጠን ይህ የተርን ኦቨር ታክስ ማሠልጠኛ ሞጁለ ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህ ሞጁል ግልፅ የሆነ የታክስ ትምህርት በመስጠት ታክስ ከፋዮች ስለ ተርን ኦቨር ታክስ ምንነት ላይ በቂ እውቀት እንዲኖር ለማድረግ በሶስት ክፍል የተከፋፈለ የተርን ኦቨር ታክስ ማስተማሪያ ሞጁል እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ሁኔታ

### 1.1 ዓላማ

የሞጁሉ ዋና ዓላማ፤

በዚህ ሞጁል የሚሠለጥኑ ሠልጣኞች በሥልጠናው መጨረሻ:-

የሥልጠና ሞጁሉን በቲኦቲ አዋጅ ቁ. 308/2002 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁ. 611/2008 መሠረት በማቅረብ እና በመወያየት የቲኦቲ ምንነት ተረድተው እና አውቀው የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ።

## 1.2 የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማ፤

በሞጁሉ ሥልጠና ሂደት ሠልጣኞች:-

- የተርን ኦቨር ታክስ ምንነት ይገልጻሉ፤
- የተርን ኦቨር ታክስ **የሚመለከታቸው መሆናቸውን አውቀው የታክስ መብት እና ግዴታቸውን ይዘረዝራሉ፤**
- የተርን ኦቨር ታክስ  ሚመለከታቸው እና የማይመለከታቸው ግብይቶች ይለያሉ፤
- የተርን ኦቨር ታክስ **ምጣኔዎቹን ይዘረዝራሉ፤**
- የተርን ኦቨር ታክስ የሚሰላበት የዋጋ መሰረት አውቀው ያሰላሉ።
- አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶችን ይዘረዝራሉ ።

## 1.3 ከሥልጠናው የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ሥልጠና በኋላ ሠልጣኞች፡-

- በአዋጅ ቁ.308/2002 እና በተሻሻለው 611/2008 ስለ ቲኦቲ የተገለፀው በመረዳት የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ ያስችላቸዋል።
- ለያንዳንዱ የግብር ከፋይ ደረጃ የቲኦቲ ማሳወቅያ ጊዜ በማወቅ ግብራቸውን በወቅቱ እንዲከፍሉ ያስችላቸዋል።

## 1.4 የሥልጠናው ወሰን

የማሠልጠኛ ሰነድ ሽፋን

በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁ. 308/2002 እና በተሻሻለው 611/2008፣ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 መሠረት ይሆናል።

## 1.5 የሥልጠናው ተሳታፊዎች

የፌደራል ግብር ከፋይ ሆነው ቲኦቲ ታክስ የሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች የሆኑ ሁሉ ይሠለጥናሉ።

## 1.6 ሥልጠናው የሚወስደው ጊዜ

ይህን ሰነድ ለማሠልጠን ሶስት ሰዓት ያስፈልገዋል::

## 1.7 ትርጉም

- ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ማለት፡- ወጪ ተቀናሽ ሳይደረግ ጠቅላላ ገቢ ሲሆን የተሸጡት ዕቃዎች የተመረቱበትን ወይም የተገዙበትን ዋጋ ይጨምራል ።
- ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ማለት ፡- ከተርን ኦቨር ታክስ ነጻ ከተደረገው በስተቀር በንግድ ስራ ሂደት ወይም የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ለማሻሻል የሚደረግ ጥረት ዕቃዎችን ማቅረብ ወይም አገልግሎቶችን መስጠት ነው ።
- ታክስ ማለት ፡-የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ ነው ።

- ታክስ ከፋይ ማለት፡- የተርን ኦቨር ታክስን ሰብስቦ ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው ።
- ዕቃ ማለት ፡- የልውውጥ ዋጋ ያለው ጠቀሜታ የሚሰጥ ወይም ፍላጎት የሚያሟላ ማናቸውም ዕቃ ወይም ሸቀጥ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል።
- ሽያጭ ማለት፡- ዕቃዎችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት መገበያየትና የተወሰነ ክፍያ መቀበል አገልግሎስ መስጠት ሲሆን ታክስ ከፋዩ ያለክፍያ የሚሰጣቸው ዕቃዎችን ወይም የሚያቀርባቸውን አገልግሎቶችን ይጨምራል ።
- አገልግሎት ማለት፡- የእቃዎችን ዝውውር የማይጨምር በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው ።
- ድርጅት ማለት ፡- የንግድ ስራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማህበር ወይም ከሽርክና ማህበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር የህግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን በውጭ አገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ የሚያከናውን ወኪልና ፀንቶ በሚሰራበት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ህግ የተመሠረተ እውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል ።

# ክፍል ሁለት

# ተርን ኦቨር ታክስ

## 2.1 የተርን ኦቨር ታክስ ምንነት

ተርን ኦቨር ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ ታክስ አይነቶች የሚመደብ የታክስ አይነት ሲሆን ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ግብር ከፋዮች በአገር ውስጥ በሚከናውኑት ግብይት ወይም አገልግሎት ነጻ ከተደረጉት በስተቀር የዕቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ወቅት በየደረጃው የሚጣል የታክስ አይነት ነው።

## 2.2 የታክሱ መጣኔ

- በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ 2% (ሁለት በመቶ)፣
- በአገር ውስጥ በሚሸጡ አገልግሎቶች ላይ ፣
  - *ሥራ ተቋራጮች*፤የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ የትራክተሮች እና ኮምባይን ሀርቨስተሮች አገልግሎት 2% (ሁለት በመቶ)፣
  - በሌሎች አገልግሎቶች 10% (አስር በመቶ)

## 2.3 የታክሱ ስሌት መሠረት;

- ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው ።
- ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በሽያጩ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ከገዢው ሰብስቦ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

## 2.4. ከታስ ነፃ ስለመሆን

❖ ከተርን ኦቨር ታክስ ክፍያ ነፃ ግብይቶች :-

- ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ የመኖርያ ቤት ሽያጭ እና የመኖርያ ቤት ኪራይ
- የፋይናንስ አገልግሎቶች
- ለሳንቲሞችና መዳልያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦች እና የዋስትና ሰነዶች ማሰራጨት
- በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከአምልኮ ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች
    - የሕክምና አገልግሎቶች እና አግባብ ባለው የመንግስት መሥርያ ቤት በሚወጣ መመርያ መሠረት ነፃ የተደረጉ አገልግሎቶች
    - በትምህርት ተቋሞማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች እንዲሁም ለሕፃናት ጥበቃ በመዋእለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች
    - ለሰብአዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣ የኤሌክትሪክ፤የኬሮሲን እና የውሃ አቅርቦት፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች
    - ማንኛውም የስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግስት የሚሰጥ ክፍያ
    - ከ 60% በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት የሚቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች
    - መፃሕፍት( ወደ ሀገር የሚገቡ፣ በሀገር ውስጥ የሚሸጡ እና መጻህፍትን ወቅታዊ ለማድረግ የሚወጡ እትሞች )
    - የምግብ እህል ( ጤፍ፤ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዘንጋዳ ፣ዳጉሳ ፣ አጃ፣ እንዲሁም የነዚህ ዱቄት ከጥራጥሬ አተር ፣ባቄላ፣ምስር ፣አኩሪ አተር፣ሽንብራ ፣ግብጦ ፣ጓያ )
    - የቅባት እህሎችም ሆኑ ፕሮሰስ የተደረጉ ምግቦች፣ ፋርሽካም ጭምር የታክስ መነሳት አይመለከታቸውም ።

**<u>ምሳሌ፡-</u>** አቶ አበበ በሸቀጣ ሸቀጥ እና በእህል ንግድ ስራ የተሰማሩ ሲሆን የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ሰራቸው 300,000 ብር በእህል ንግድ 180,000 ብር ጠቅላላ ሽያጫቸው 480,000 ብር ቢሆን

1. የሚሰበሰቡት ተርን ኦቨር ታክስ ስንት ይሆናል?
2. ታክስ የማይሰበሰብበት ገቢ ስንት ነው ?

<u>መልስ</u>

➢ ታክስ የሚከፈልበት የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ

300,000 x 2% = 6,000.00

➢ የእህል ንግድ ከተርን ኦቨር ታክስ ነጻ በመሆኑ ታክስ አይሰበሰብበትም

## ክፍል ሶስት

## 3.1 ታክሱን ማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት

- ታክስ ከፋዩ የታክስን ስሌት በትክክል የማከናወን፣የታክሱን ማስታወቅያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ የማቅረብና ታክሱን በጊዜው የመክፈል ኃላፊነት አለበት ፡፡
- የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች እያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣን ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቅያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወድያውኑ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

### 3.1.1 የሂሳብ ጊዜ ማለት

- በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 የደረጃ ‹ሀ› ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ
- የሂሳብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ ‹ለ› ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ የበጀት አመት ወይም የታክሱ በለሥልጣን ሲፈቅድ በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ የመጀመርያው ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የሶስት ወር ጊዜ
- በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 በተደነገገው መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ ‹ሐ› ግብር ከፋዮች የበጀት ዓመቱ ነው ፡፡

### 3.1.2 የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን

- የታክስ ከፋዩ ሂሳብ ከተመረመረ በኋላ ሊከፈል የሚገባው ታክስን አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የታወቀ ከሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ይሰጣል
- ታክስ ከፋዩ የሂሳብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ በማናቸውም ምክንያት በታክስ ባለስልጣኑ እንዲያቀርብ ተጠይቀ ካልቀረቡ ወይም የሂሳብ መዛግብትና ሠነዶች ከሌሉየታክስ ባለስልጣን ታክሱን ባለው መረጃ ወይም የዕቃውን ወይንም የአገልግሎት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይወሰናል

**<u>ማስታወሻ፡-</u> የሁሉም ታክሶች አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ህግ በአንድ ላይ ተጠቃሎ በአዋጅ 983/2008 ቢኖርም ለዚህ ሰነድ የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 611/2008 ጨምሮ አዋጅ ቁጥር 308/2002 ላይ የተደነገጉት አስተዳደራዊ እና የወንጀል ድንጋጌዎች ላይ የተገለፁ ቅጣቶችን በተጨማሪነት ማየት ያስፈልጋል፡፡**

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ፣ ሞጁሉ በሶስት ክፍሎች የተርን ኦቨር ታክስ የተዳሰሰ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ ሁኔታ ቀርቧል። በሁለተኛው ክፍል የተርን ኦቨር ታክስ ምዝገባና ስረዛን የሕግ መሠረትና ታሳቢዎች፣ ይዘትና አፈጻጸም የያዘ ነው። በክፍል ሦስት የታክሱ አስተዳደርና ሪፖርት የማደረግ ኃላፊነቶችን በተመለከተ በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ 308/2002 ላይ የተደነገጉ ድንጋጌዎችች ይዳስሳል። በመሆኑም እነዚህን የተርን ኦቨር ታክስ ድንጋጌዎች በመከተል ግብር ከፋዩቻችን ግዴታዎን በመወጣት መብትዎትን ይጠይቁ ዘንድ አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣሉ።

የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች ተብሎ  የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ፤ የሂሳብ መዝገብ ለሚይዙ የደረጃ "ለ"ታክስ ከፋዮች በግብር መክፈያ /ሂሳብ ጊዜአቸው ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር በየሶስት ወር ጊዜ እና የሂሳብ መዝገብ ለማይይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ታክሱን አሳውቆ መክፈል ይጠበቅባቸዋል ፡

## ማጣቀሻ

የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁ. 308/2002 እና በተሻሻለው 611/2008፣ የገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 እና የታክስ አስተዳደር አዋጅ 983/2008 ነው ።